# ኢህአዴግ ከታሪክም ይታራቅ ?!

ብርሀኑ በረሐ

‹‹ከትግራይ እስከ ደቡብ ጫፍ ሕዝቡ ተመሳሳይ ቅራኔ ፈጥሯል በአንዳንድ አካባቢ በእጁ ዞር በሉ ብሎናል ችግሩን በመፍታት ከሕዝቡ መታረቅ አለብን ››
ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ቃል ክቡር ነው ለታሪክ ና ለህዝቦች ሉአላዊ ሙብት !!!

ቃል ክቡር ነው ስለሆነም ሁሌ እውነትን መሰረት ማድረግ ለቃል ጌጡ ነው ቃል ብውሸት ሲከናነብ ግን ይረከሳል ክብሩ ይጠፋል፡፡ ቃል ከእግዜአብሄርና በሱ ምስል ከተፈጠረው ከሰው ብቻ ይወጣል፡፡ የቃል ክቡርነት ምንጩም ይህ ነው፡፡ ኢህአዴግ በኤርትራና በኢትዮጵያ ጉዳይ የፈፀመው ስህተት ግዙፍ ነው የተሳሳተ ቃል ወጥቶበታል ተግብሮታልም፡፡ ስለዚህ ቢያንስ ለታሪክ ከታሪክ መታረቅ ያስፈልገዋል መታረቁ ካልቀረ፡፡ ታሪክ ሰሪው ህዝብ ነውና ከታሪክ መታረቅም ከህዝብ መታረቅ ነውና ፡፡

1. በኤርትራ ጉዳይ የባለ ራእዩ መለስ ዜናዊ/ የኢህአዴግ ቃል
“ ለ/ ሕጋዊ ሁኔታው
ኤርትራ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ከመዋሏ በፊት እንደማንኛውም የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ሁሉ የኤርትራ ጉዳይም ወደ ተባበሩት መንግስታት ቀርቦ ነበር። ዳሩ ግን በወቅቱ የተባበሩት መንግስታት ውስጥ በነበረው የኣመሪካ ኢምፒሪያሊዝም የበላይነት ሳቢያ የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት ምን እንደሆነ ሳይጠይቁ “ከኢትዮጵያ ጋር እንዲያብር” ተገደደ። ይህ በሚሆንብት ጊዜ ግን የድርጊቱ ኣፈፃፀም ሁኔታ የተከተለው ኣንድ “ሕጋዊ” ኣግባብ እና መንገድ ነበር። ውሉ ኢትዮጵያንና ኤርትራን ሁለት የተለያዩ ኣገሮች እንደሆኑ በውሉ ተቀብሎ በመካከላቸው የሚደርገው ውልም የፌደረሽን ውል እንደሚሆን ይጠቁማል።በተጨማሪም ማንኛውም ወገን/ሃይል/ የተባበሩት መንግስታት ሳያስታውቅ ወይም ሳያስፈቅድ ውሉን ማፍረስ እንደማይችልም ይጠቁማል፤/ የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት፤(ግምገማ) (1979 ዓ.ም) (ገፅ 9-10)
የኢህአዴግ ቃል
ኢህአዴግ በመጀመርያው የፖለቲካ ፕሮግራሙ በ ገፅ 43 “…… ሀ) የኤርትራ ጥያቄ በኣፈጣጠሩና በታሪካዊ ኣመጣጡ የባዕዳዊ ቅኝ ኣገዛዝ ጥያቄ ነው። “ በማለት አቋዋሙን አስረግጦአል፡፡

2. የተባሩት መንግስታት ቃል
ሀ/ የተባሩት መንግስታት ቅድመ ውሳኔ ጥናት
General Assembly of the United Nations adopted Resolution 289 A (IV) on November 21, 1949, established a commission to investigate and make proposals according to the terms of reference given by the Assembly.
(a) The wishes and welfare of the inhabitants of Eritrea including the views of the various racial, religious and political groups of the provinces of the territory and the capacity of the people for self-government
(b) The interests of peace and security in East Africa
(c) The rights and claims of Ethiopia based on geographical, historic, ethnic and economic reasons including in particular Ethiopia’s legitimate need for adequate access to the sea.
ሁ/ የተባበሩት መንግስታት የጥናት ውጤት
“ጥናቱ 44.8% የሚሆነው ህዝብ የኣንድነት ማሕበርን እንደሚደገፍ ሲግልፅ 40.5% ራቢጣ እስላሚያን 4.4% ሊበራል ፓርቲ 9.2% ፕሮ ኦታልያ 1.1% ኣንድን የእንግሊዝን ኣስተዳደር መቀጠል የሚሻ ትንሽ ፓርቲ ዳግፎአል።” ይህ መረጃ ኢህኣዴግ “ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ በኤርትራና በአንድነት ጥያቄ” /1984 ዓ/ም በሰነዱ ያሰፈረው ከኢህአዴግ የማያከራክር መረጃ ነው ብየ እገምታሁ ወደ ሁዋላ ተመልሰን ስናየው ያከራከራል ካልተባለ፡፡
ሂ/ የተባበሩት መንግስታት ውሳኔ
“ON December 1950, the general assembly resolution 390A (V) which recommended that Eritrea shall constitute an autonomous unit federated with Ethiopia under the sovereignty of the Ethiopian crown”
አስተያየት
1. የኤርትራ በፌደረሽን ከኢትዮጵያ መቀላቀል በኢትዮጵያ ጥያቄ በተባሩት መንግስታት ውሳኔ የተቋዋጨ እንጂ ኤርትራን በመወከል ከኢትዮጵያ በፌደረሽን ለማበር የተዋዋለ የኤርትራ መንግስት ወይም ወኪል አልነበረም ፡፡ኤርትራም መንግስት አልነበረችምና ከኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ውል ለመፈረም የሚያስችላት የሕግ ችሎታ / International LegaL Personality / አልነበራትም፡፡

2. የፌደረሽን ውል ባልነበረበት ውሉን ማፍረስ የፈለገ አስቀድሞ የተባበሩት መንግስታት ማሳወቅ አለበት የሚል ግጼታ ሊኖር አይችልም አልነበረምም፡፡
3. የተባበሩት መንግስታት ውሳኔ ከላይ እንደተመለከተው ሆኖ under the sovereignty of the Ethiopian crown" የሚለው ግልፅ ነው የሁለት ሃገር ስብእና ሳይሆን የአንዲት ሉእላዊት ሃገር/ኢትዮጵያ/ ሉእላዊ ስብእና ነው የሚናገረው፡
4. የሁለት ሃገራት ውል እንደሌለ እያወቅኩኝ እነዳው ለሌላ ሃሳብ ክፍት ለማድረግ ፡- የተለያዩ ሃገራት እንደሆኑ የሚጠቁመው የውል ቃል አልነበረም በእርግጠኝነት አልነበረም አለ የምትብሉ የሁለት ሃገራት ስምምነት ከነበረ እስኪ ኤርትራን በመወከል የፌደሬሽን ስምምነት የፈረመው የኤርትራ ሉእላዊ ባስላጣን ይነገረን ? እስኪ ሰነዱም ይጠቀስልን ለህዝብ ይፋ ይሁን ?
ሃ/ በፌደረሽኑ የህዝቡ ፍቃድ በተመለከተ
የተባበሩት መንግስታት የህዝቡ ፍላጎት ለማወቅ የተከተለው መንገድ ህዝቡ በወቅቱ ለነበሩ ፓርቲዎች የነበረው ድጋፍ መሰረት ያደረገ ነበር፡፡
"ጥናቱ 44.8% የሚሆነው ህዝብ የኣንድነት ማሕበርን እንደሚደገፍ ሲግልፅ 40.5% ራቢጣ እስላሚያን 4.4% ሊበራል ፓርቲ 9.2% ፕሮ ኦታልያ 1.1% ኣንድን የእንግሊዝን ኣስተዳደር መቀጠል የሚሻ ትንሽ ፓርቲ ዳግፎኦል።" በዚህ መረጃ ኢህአዴግም ልዩነት እነደሌለው ከዛም አልፎ የኤርትራ ህዝብ ፍለጎት ነፃነት እነደነበረ "በኣጠቃላይ ሲታይ 44.8% የህብረት ደጋፊዎች 54% የነፃነት ደጋፊዎች ወይም ኢንዲፐንደስ ብሎክ 1.1% የኢንግሊዝ ደጋፊዎች ነበሩ" በማለት ደጋፊ መረጃ አድረጎ ሞግቶአል፡፡
አስተያየት
1. በእርግጥ ህዝቡ ለፓርቲዎች ከሚሰጠው ድጋፍ አንፃር የህዝቡ ፍላጎት ለመገመት አያስችልም አይባልም የዳሰሳው ውጤት ሲተረጎም የተባበሩት መንግስታት ውሳኔ ይደግፋል፣ የኤርትራ የሃገር ማንነት እንዳልነበረም ግልፅ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም
- ማሕበር አንድነት የተባው ፓርቲ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ መቀላቀል የሚል አቋዋም የነበረው ፓርቲ ከሁሉም ፓርቲዎች የላቀ 44.8% ድጋፍ በማግኘቱ
- ከኢትዮጵያ ጋር በመደራደር ከኢትዮጵያ ጋር ማበር/ የተወሰነ ቅድመ ሁኔታ ኣሟልቶ መተባበርን የሚል ኣቋም የያዘ ሊበራል የህብረት ፓርቲ በማለት ኢህአዴግ ራሱ የሚገልፀው ሊበራል ፓርቲ 4.4% ያገኘው ድጋፍ በነፃነት ፈላጊነት ሊደመር የሚችል በላመሆኑ ይደመር ከተባለው የአቋዋሙ ይዘት ከአንድነት ሃይል የሚደመር መሆኑ፣ምክንያም አንዳንዴም ከአፄ ዮሃንስ 4 ኛ ዘር የወጡ ራስ ስዩም መንገሻን ንጉስ በማደርግ የትግራይ ትግርኝ መንግስት መመስረት እንደሁለተኛ አማራጭ ሲያራምድ በ 1946 ከኢትዮጵያ በፌደረሽን ለማበር የሚል ከማህበር አንድነትም ስምምነት ደርሶ የነበረ በመሆኑ፡፡/ተስፋፅዮን 1986፣14/
-ኢህአዴግ ራቢጣ እስላሚያ ለዓረብ ፖለቲካ እንጂ ለኤርታራ ነፃነት ያልቀመው ፣ፕሮ ኢጣልያ ለኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ እንጂ ለኤርትራ ነፃነት ባልቆመበት የማሕበር አንድነት ፓርቲ ከፍተኛው ድምፅ ለማንኩዋሰስ የኤርትራ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በአሸባሪነት በመክሰስ ማጣጠሉና የውጭ ሃይሎች ተላላኪ ቡድኖች የነፃነት ብሎክ ብሎ መፈረጁ ታሪካዊ ስሕተት ፈፅሞአል፡፡
- ይሀ ስህተት የአፍሪካ ፀረ ቅኝ ገዥዎች የነፃነት ቀንዲል የተባለቸ ኢትዮጵያ የኤርትራ ቀኝ ገዥ ወደሚል ግዙፍና መሰሪ ስህተት ኢትዮጵያን በቅኝ ገዠነት ወንጀል አሰለፋት፡፡
- ይህም በተራው የኤርትራ ጥያቄ የነፃነት ጥያቄ ነው ለማለት ተጠቀሙበት፣ከዚህ በመንደርደር ኢትዮጵያ የባህር በር የግዛት ሉእላዊነት መብትዋን ድምጥማጡ አጠፋ ፡፡
ሄ. ኤርትራ የኢትዮጵያ ሉእላዊ ግዛት ካልነበረች ?
የኢህአዴግ ቃል
"ኤርትራ የኢትዮጵያ ኣካል ነበረች፤ነች፤ የሚለው ኣባባል ምንም ዓይነት ታሪካዊ መረጃ የማይገኝለትና የሌለው "ኣፈ ታሪክ" ሆኖ ኢትዮጵያ ራሷን የቻለች አንድ ሃገር ሆና በቆመችበት ወቅት ኤርትራ የኢትዮጵያ ኣካል ኣልነበረችም። በኣንፃሩ በኢጣልያ ቅኝ ግዛት ሥር የተፈጠረች ኣገር ነች። በአፍሪቃ የኣገሮች ኣፈጣጠር ታሪክ ኣኳያ ሲታይ ኤርትራ የኢትዮጵያ ኣካል ስትሆን ኬንያ፤ ጋና .....ወዘተ እንደመሳሰሉት ማንኛውም የኣፍሪካ ሃገር ሁሉ ከተመሰረቱበት ሁኔታና ኣገባብ መሠረት ልዩ ባልሆነ ሁኔታና ኣገባብ የተመሠረተችና ከኢትዮጵያ የተለየች ራሷን የቻለች ኣገር ናት"
/የኤርትራ ጥያቄ ከየት ወዴት በ 1979 ዓ.ም፣ ገፅ 8 በአቶ መለስ ዜናዊ ተፅፎ በህ.ወ.ሓ.ት/ማሌሊት ተገምግሞ በኢህአዴግ ቆርቦ ስጋሁ ወደሙ የለበሰው /
የተፈፀመው ስህተት ይበልጥ ግልፅ እንዲሆን በጥያቄ ማቅረቡ መርጫሉኝ እንሆ !
1. ኢትዮጵያ ከቱርኮች ከግብፆች ከጣልያኖች ሃገርን የመከላከል መራራ ጦርነቶች ለምን አካሄደች ? አፄ ቴውድሮስ ፣ አፄ ዮሃንሰ ወራሪ ነበሩ ጦርነቱ በሁለት ወራሪ መንግስታት የተካሄደ ነበር ?
2. ኤርትራ የኢትዮጵያ ሉእላዊ ጋዘት ካልነበረች ኢጣልያ ከአፄ ምንሊክ የውጫሌ ውል መፈራረም ለምን አስፈለጋት ለምንስ ሚኒሊክ የውጫሌ ውል በመፈረማቸው ተወቃሽ ይሂናሉ ?
3. ኤርትራ የኢትዮጵያ ሉእላዊ ግዛት ካልነበረች አፄ መኒሊክ ከአድዋ ድል በሁዋላ ኢጣልያን ከኤርትራ ጨርሶ ለማባረር በተለይ ከራስ አሉላ የቀረበላቸው ሃሳብ ባለመቀበላቸው ተወቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ ?
4. ኤርትራ የኢትዮጵያ ሉእላዊ ግዛት ካልነበረችና ከኢትዮጵያ አብራ የተፈጠረች ሃገር ከነበረች አፄ ምኒሊክ በተደጋጋሚ ከኢጣልያ እየዋዋሉ አሰልፈው በሰጡት ግዛት ለምን የታሪክ ተወቃሽ ይደረጋ ?

5. ኢትዮጵያ እንደሃገር የቆመችና በዓለም አቅፍ ደረጃ ታዋቂ ሃገር የሆነች ጥንታዊት ኦሪታዊት ሃገር እነጂ በአፍሪካ ቅርምት ዘመን የተፈጠረች ባልሆነበት ከሶማሊያና ከኬንያ ማመሰሰል ምን ያክል የታሪክ ሎጂክነት አለው
ሀ/ ከኢትዮጵያ የመገንጠል አጀንዳ የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት ነበር ?
ዶ/ር ተስሃፅዮን መድሃንየ የተባሉ ኤርትራዊ 'The Dynamics of Eritrean National Question, B.R.Gruiner. Amastardam,1986 በሚል መፅሓፋቸው ገፅ 31 ላይ እነዳሰፈሩት የመጀመርያው የኤርትራ የነፃነት ጥያቄ ያነሳ ጀብሃ በምዕራብ ኤትራ መጀመርያ በግለሰብ ደረጃ በሽፍትነት እያለ የ ሶርያና ኢራቕን ወታደራዊ ኤክስፐርት በ ቆላ ኤርትራ በመገኘት እነዳደራጁአቸው na የኤርትራ ህዝብ ድጋፍ አልነበረውም፡፡ ጀብሃ የመጀመርያ ድርጅታዊ ጉባው በ 1971 በሰሃል በረሃ ሲያካሄድ ከዚህ በፊት ጀብሃ የፖለቲካ ፕሮግራም የሚባል አልነበረውም፡፡ በዚሁ ጉባኤ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ለመሆን የሚያስችላት እድገት ስላይደለች በኢትዮጵያ ውክልና የሚፈፀም የተባበሩት አመሪካ ኢምፔሪያለዝም ጭቆና ነው ያለን ብለው ስሙም ልዩ ቅኝ አገዛዝ/ Special colony/ አሉት፡
1.ጀብሃ በመጀመርያ ድርጅታዊ ጉበኤው ሲያካድ የኤርትራን ማሕበረሰብ የነፃነት ደጋፊ ብሎ የገለፀው አልነበረም ብቻ ሳይሆን የኤርትራ ከበርቴ የነፃነት ጠላት በማለት የኤርትራ ገበሬና ዘላን ያልነቃ በጉዳዩ ምንም ስሜት እንዳልነበረው ደገኛው ክርስትያን ግድጋፉን ለክርስትያኑ የሃይለስላሴ መንግስት እንደሚያደላና ወዝአደሩና ሙሁሩም ለነፃነት ትግሉ ድጋፋቸውን እንዳላሳዩ ነበር የሚያትተው ፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ታድያ የኤርትራ የነፃነት ጥያቄ የተሸፈነው የማን ፍላጎትና ጥያ ነበር ብሎ መጠየቅ ምክንያታዊ ነው፡፡
2. የሃይለስላሴ መንግስት ወድቆ በኤርትራው አማን ዓምዶም የሚመራ ወታደራዊ መንግስቲ እነደቆመ ጀኔራል አማን ዓንዶም በ ኤርትራ ምድር በመገኘት ለአንድነት ያደረገው ቅስቀሳ በረሃ ገብቶ የነበረው በወላጆች ጫና በተለይ በደጋው ኤርተራ በብዛት ይመለስ እንደነበረ ኤርትራዊው ደክተር ተስሃፅየን መድሃንየ የረጋግጡ ፡
3. በደርግ ጅላጅል ፖለቲካ ጀኔራል አማን ዓምዶም በመገደሉና የደርግ ጭካ በማየሉ ቅሬታው አገርሽቶ ተቃውሞው ቢበረታም የኤርትራ የቃዋሚ ድርጅቶች ከነፃነት በታች ከኢትዮጵያ መንግስት በመደራደር በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ስር ለመስማማት ተቃርበው እንደ ነበረ በኢህአዴግም የሚታመን ሃቅ በመሆኑ የኤርትራውያን በአንድነት የመኖር ፍላጎት በትጥቅ ትግሉም የተሙዋጠጠ አልነበረም፡፡
- ኢህአዴጎች ይህንኑ ግዙፍ ስህተታቸው አልተገነዘቡትም ብየ አልደፍርም የከበዳቸው በዚሁ አቁዋማቸው ከተከፋ ህዝብ የመታረቁ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ቅን የፖለቲካ ቁርጠኛነት ይጠይቃል ፡፡
መታረቅ ከተፈለገ ከታረክም መታረቅ የብልሆች ነው !!!
ሪፖርተር